# ውረድ ወደ መሬት በቀስተ ደመና(ተስፋሁን ሞላ)



ውረድ ወደ መሬት በቀስተ ደመና፤

ፍጥረትክን ገላግለው ከዲያብሎስ አፈና።

ከቤተ ክርስቲያን እስከ መስጊድ ቅጥር፤

ዙሪያውን ከቦታል የዲያብሎስ ወታደር፤

በህዝቡ ላይ ጭኗል አሰቃቂ ቀንበር፤

ኢትዮጵያን ታደጋት የፈጠርካት እግዜር።

ውረድና ፍረድ ኢትዮጵያን ገላግላት፤

ካላንተ በስተቀር የለም ሚታደጋት፤

በአንተ እያመለከ የኖረው በአንድነት፤

እስላም ክርስቲያኑ ተሰቃየ በእውነት።

ሰራዊትህን ልከህ ኢትዮጵያን ጠብቃት፤

ጨርሰው እንዳይጠፉ የእምነት ተቋማት፤

የባህታዊ ፤ መኖሪያ ፤ የመነኮሳት፤

ሌት ተቀን ወደ አንተ የሚጸለይበት፤

ታሪካዊ ቦታ ፤ ገዳም ፤ አድባራት።

እጆቿን ዘርግታ ወደ አንተ ታያለች፤

እባክህ ፈጣሪ ተመልከት ወደ ታች፤

የምትመጣበቱን መንገዱን አመቻች።

ተሎ ፍረድ እንጂ ሳትውል ሳትዘገይ፤

እንባዋን አብሰው ሁነህ ከሰማይ።

እጆቿን ዘርግታ ወደ አንታ ቀርባለች፤

በሩን ከፈትላት ትስገድ ከግርህ በታች፤

ብቻዋን ቀርታለች ልጆቿ ተባርው ከሀገር፤

የደረሰባትን ብሶቷን ችግሯን ትናገር፤

ለኃያሉ ጌታ ለአንተ ለፈጠርካት እግዜር።

ልጆቿ ተባረው ብቻዋነን ቀርታ፤

ወደ አንተ ቀርባለች ወደ ኃያሉ ጌታ፤

ሰማዩን እያየች እጆቿን ዘርግታ፤

ተለመናት እንጂ ፊትህን አታዙር፤

ታውቀዋለህና የወላድን ችግር፤

በአንተ እናት አይተሃል የደረሰውን መሪር፤

ተገፍታ ስትወጣ ከእስራኤል ምድር፤

አንተን አቅፋ ስትንከራተት ከሃገር ወደ ሃገር፤

አይተሃል እንባዋን ስታለቅስ ከምር፤

አንተ ምስክር ነህ አብረህ ቁመህ ነበር።

ማርያም ተመለሰች ከስደት ወደ ሀገር፤
አሳዳጇ ጠፍቶ ከእስራኤል ምድር፤
የእምዬስ በዛባት አመታት አስቆጠረ፤
ከስደት ላይ ስደት ስደቱ ጨመረ።

የእምዬ አሳዳጅ ሲወርድ ፤ ወደ መቃብሩ፤
ሌላ አሳዳጅ  መጣ ተተክቶ በእግሩ፤
ሕዝቡን የሚያፈናቅል ከቀየ ከሃገሩ፤
እየባሰ ሄደ በዛባት መካራው ችግሩ።

የምታበላቸው ስታጣ እራትና ምሳ፤
በቤቷ ውስጥ ነግሶ የረሃብ ነቀርሳ ፤
ሞት ምድሪቱን ሞላት በልጆቿ እሬሳ።

ተሎ ፍረድ እንጂ ሳትውል ሳትዘገይ፤
እንባዋን አብሰው ሁነህ ከሰማይ፤
ረሃብ ጎድቶአቸው ሲወድቁ ሜዳ ላይ፤
እስከ ህይወታቸው ሆኑ ለአሞራ ሲሳይ።

ችግሯ ሲበዛ የተናገርከውን ቃልህን አስታውሳ፤
ወደ አንተ ዞራለች እንባዋን አፍስሳ ፤
ከመሬት ላይ ወድቃ ፤ ከፍቷት አመድ ለብሳ።

እያየህ ዝም አትበል የፈጠርካት ጌታ፤
እንባዋ ሲፈስ ጧት ይዞ እስከ  ማታ፤
አቁመው እንባዋን ውረድና አንዳፍታ፤
መከራዋም ይብቃ ይቀየር በደስታ።

እባክህ በቃሽ በላት የፈጠርካት እግዜር፤
መከራዋ ሁሉ በደስታ ይቀየር፤
ልጆቿ እንዲኖሩ ተስማምተው በፍቅር።

ቋንቋ ሳይለያቸው እንዲሁም ሃይማኖት
ጠይሙ ከጥቁሩ አብረው ከኖሩበት፤
በወንድማማች በኢትዮጵያዊነት፤
ተሳስበው ከኖሩት ለረጅም ዘመናት፤
የሚከፋፍል መጥቶ የተኩላ መንግሥት፤
በልጆቿ ደም ኢትዮጵያን አጠባት።
ልጆቿን ጨርሶ እሷንም ሊውጣት፤
ዘንዶው አፉን ከፍቶአል ተሎ ድረስላት፤
የኢትዮጵያ አምላክ የዓለም መድኃኒት።

16/04/2013